# ቅንጅት ከማንም ከምንም በላይ ነው ።

December 24 – 2007

ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ሰላም ተጠብቆ ዲሞክራሲ ዳብሮ የዜጎች መብት በሙሉ ተከብሮ ልማት ተጠናክሮ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የዳቦ ቅርጫት ትሆናለች የሚለውና ለብዙ ዘመናት ሕልም ሆኖ የቀረውን እውን ለማድረግ ቆርጠው በተነሱ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ ፈቃደኝነትና ፍላጎት ውህደት የተመሰረተ ሲሆን እነዚህ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ትንሳኤን ለማፋጠን
እንደ አንድ አካል ሆነው በመቆም በ1997 ዓ . ም በተካሄደው ምርጫ ፈጣን እንቅስቃሴ በማረግ በኢትዮጵ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ መልኩ በመላው የኢትዮጵያ ክልሎች በማሸነፍ የሕዝብ ድጋፍ ያለው የፖለቲካ ፓርቲ በሰላማዊ ትግል የመንግሥትን ሥልጣን ከአምባገነኖች መረከብ እንደሚችል ለነፍጥ አምላኪዎች የማይረሳ ትምህርት ለመስጠት የበቃ ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲ መሆኑን አረጋግጧል ።

ይሁን እንጂ በምርጫው ያገኘው ድል በሀይል መነጠቁ ሳያንሰው ሕልውናው ጨርሶ እንዲጠፋ አመራሩ ወህኒ እንዲገባ በመደረጉ የድርጅቱ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ቀዝቅዞ በኢትዮጵያ ውስጥ የፈጠረው አሉታዊ ጫና ቀላል ባይሆኑም በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሠላማዊ ትግላቸውን በማስተባበር የዓለም ሠላም ወዳድ ሕዝቦችን ከጎናቸው እንዲቆሙ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ጥረት በማድረጋቸው አመራሩ ከእስር ለመለቀቅ በመቻሉ የድርጅቱን ፖለካዊ እንቅስቃሴ ወደነበረበት ለመመለስ ይቻል ዘንድ ልዑካን ወደ ተለያየ የዓለም አገሮች ሲልክ ወደዚህ ወደ ሰሜን አሜሪካም አምስት አባላት ያሉበት አንድ የልዑካን ቡድን መላኩ የሚታወስ ሲሆን ቡድኑ የተላከበትን ሀላፊነት ወደ ጎን በመተው ከተሰጠው መመሪያ ውጭ ከመንቀሳቀሱም በላይ ድርጅቱን ለማፍረስ አሉታዊ ተግባር እየፈጸመ የሚገኝ መሆኑን በመግለጽ የድርጊቱ ፈጻሚ አምስት ከፍተኛ አባላት ከታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ . ም ጀምሮ በቅንጅት ስም ከሚያደርጉት ማንኛውም ተግባር እንዲታቀቡና ይህንንም የሚመረምር ኮሚቴ ተቋቁሞ ውጤቱን ለጠቅላላ ጉባኤ እንዲያቀርብ የሚጠይቅ የድርጅቱ መሪ ኤንጂነር ሀይሉ ሻውል ለቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት ከጻፉት ማሳሰቢያ ለመረዳት ችለናል ።

ግለሰቦቹ ፈጸሙ የተባሉት አሉታዊ ተግባራት በሀያ ነጥቦች የተዘረዘሩ በመሆናቸው በቀላሉ መረዳት ስለሚቻል በድርጅቱ ውስጥ ሕዝብ ተስፋ የጣለባቸው እንዲህ አይነት ጥፋት ፈጸመው መገኘታቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ እጅግ የሚያሳዝንና የሚያስቆጣው ቢሆንም በፖለቲካ ሂደት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ሲከሰቱ የቆዩና ወደፊትም ሊከሰት የሚችል በመሆኑ የሚያስደንቅ ሊሆን አይችልም ። ምክንያቱም **እውነትና ንጋት እያደር ይጠራልና** እንግዲህ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ከየትኛውም አቅጣጫ ለሚገጥመው አፍራሽ ተግባር ለመከላከል አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ለመጥራት በሚያስችል ሁኔታ ውስጥ በሚገኝበት ጊዜ የድርጅቱ መሪ በድርጅቱ ውስጥ ባለው የመሪነት ሀላፊነት መሠረት ወቅታዊና ፈጣን እርምጃ ወስዶ
ለድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ ለማሳወቅ ቀዳሚ ተግባሩ መሆኑ ጥያቄ ውስጥ የሚያገባ አይሆንም ።

ስለዚህም የቅንጅት መሪ ኤንጂነር ሀይሉ ሻውል የወሰዱት እርምጃ ግለሰቦችን ለመጉዳት ወይም የድርጅቱ ደንብ ከሚፈቅድላቸው ሥልጣን አልፈው መሄድ ሳይሆን ግለሰቦቹ በማካሄድ ላይ ያሉትን አሉታዊ ተግባር በመግታት የድርጅቱን ሕልውናና አንድነትን ለመጠበቅና በኤትዮጵያ ሕዝብ ስሜት ላይ እየጣለ ያለውን ችግር ለማስወገድ መሆኑን ተገንዝቦ **የቅንጅ ድጋፍ መድረክ በአትላንታ** የተወሰደውን እርምጃ ከልብ ይደግፋል ።

**ቅንጅት ከማንም ከምንም በላይ ነውና ።**

**ቅንጅት በነበረው ጥንካሬ ይቀጥላል**

**ሠላምና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ይከበራል !!!!!!!!!**